# #DEFYHATENOW

# ሰላም ግንባታ እና ማህበራዊ ሚዲያ



# ሰላም በማህበራዊ ሚዲያ ዘመን

## የማህበራዊ ሚዲያ የሰላም ዘመቻ ዲዛይንዎን ሲያደርጉ፥

• ለማስተላለፍ የፈለጉት መልዕክት ምንድነው?

• ለታዳሚዎችዎ (አድማጭ/ተመልካች/አንባቢዎ) ሊስባቸው የሚችሏቸው ምን አይነት መልዕክቶች ናቸው?

• ታዳሚዎችዎ (አድማጭ/ተመልካች/አንባቢዎ) ምን አይነት የመገናኛ ዘዴ/ቻናል ይመርጣሉ?

• ቪዲዮዎችን ዩቲዩብ ላይ ማጋራት፣ ፌስቡክ ወይም ኢንስታግራም ላይ መለጠፍ?

• ታዳሚዎችዎ (አድማጭ/ተመልካች/አንባቢዎ) ማንን ሊሰሙ እና በቀናነት ሊመልሱ ይችላሉ?

• በማህበራዊ ሚዲያ ላይ እንዴት የሰላም አምባሳደር መሆን እችላለሁ?

ሰላም እንደ ግለሰብም ይሁን እንደ ማህበረሰብ ክፍል የሁላችንም ሃላፊነት ነው፤ የመንግስት ባለስልጣናት ርዕስ ብቻ አይደለም።

በዚህ በማህበራዊ ሚዲያ ዘመን ስለሰላም ስናስብ አንድ ተራ ዜጋ ምን ያህል ማድረግ እንደሚችል እና የግጭትን አቅጣጫ ለማስቀየር የያዘውን/የያዘችውን ሃይል ታሳቢ ማድረግ ጠቃሚ ነው።

**ስማርት ስልክዎትን ብቻ በመጠቀም ጭቆናን ተቃውመው መቆም ይችላሉ፤ በችግር ጊዜ ሰብዓዊ እርዳታዎችን ማገዝ ይችላሉ፤ እንዲሁም ለከፍተኛ ንቅናቄዎች አስተዋፆ/እገዛ ማድረግ ይችላሉ።**

የበይነ-መረቡ ዓለም ከበይነ-መረብ ውጪ በሆነው በገሃዱ ዓለም ላይ ያለውን ውጥረት ለማጉላት እና ለማስፋፋት ያገለግላል። በዛሬው ጊዜ የዲጂታል መድረኮች ከበይነ-መረብ ውጭም ሆነ በበይነ-መረብ ላይ ያሉ የጥላቻ ንግግሮችን ከገደብ በላይ ለማባባስ እና የበቀል ስሜትን ለማጋጋል የሚውሉ መድረኮች ሆነዋል።

ማህበራዊ ሚዲያ ሰላም ግንባታ ላይም ሆነ ሰላምን ለማፍረስ የተረጋገጠ ተፅዕኖ ያለው መሳሪያ ነው። በማስተዋል መጠቀም የእኛ ኃላፊነት ነው።